
ጋለሪያ ቶሞካ
ቴዎድሮስ መስፍንን ያቀርባል

GALLERIA TOMOCA PRESENTS **Teodros Mesfin**





ጋለሪያ ቶሞካ
አድራሻ ሳር ቤት
ከካናዳ ኤንባሲ ፊት ለፊት

**Galleria TOMOCA**
**Location: Sar Bet**
**In front of Canadian Embassy**

www.galleriatomoca.com

ጋለሪያ ቶሞካ GALLERIA TOMOCA

ቴዎድሮስ መስፍንን ያቀርባል PRESENTS **Teodros Mesfin**



"ሥዕላዊ ስላቅ እና ሥዕላዊ ምጸት"

የሥዕል ትርዒት

ጥር ፳፪ ፳፻፯ ዓ.ም.

"Cartoon & Caricature"

Art Exhibition

January 30/2015

(የፊት ሽፋን)

ሥዕላዊ ስላቅ እና ሥዕላዊ ምጸት

(On the cover)

Cartoon and Caricature

January 30/2015
Presented by Galleria TOMOCA
Art Director - Eshetu Tiruneh
Managing Director - Nebiyu Girma
Editor - Nafkot Yoseph
Printed by Central Printing Press

ይዘት

ሥዕላዊ ስላቅ እና ሥዕላዊ ምፀት ፫

ቴዎድሮስ መስፍን ፰

Contents

Cartoon and Caricature 3
Teodros Mesfin 8

# ጤና ይስጥልን!

እንኳን ወደ ጋለሪያ ቶሞካ አስራ ሦስተኛው የሥዕል ትርዒት በደህና መጣችሁ!

ንቃትንና ብርታትን የሚያጎናጽፈው ኢትዮጵያዊ ቡናችንን ቆልቶና ፈጭቶ እንዲሁም በማይቀየር ጣዕም አፍልቶ ከስድሳ ዓመታት በላይ ሲያቀርብ የቆየው ቶሞካ ቡና ኃ/የተ/የግ/ማ ለአእምሮ ንቃትን፣ ለህሊና ፈውስ የሚሆኑ የጥበብ ሥራዎችን በጋለሪያ ቶሞካ ሲያቀርብ ሁለት ዓመት ሞላው:: እነሆ ተራው የሠዓሊ ቴዎድሮስ መስፍን "ሥዕላዊ ስላቅ እና ሥዕላዊ ምጸት" የተሰኘው ትርዒት በቤተ ሥዕል ማሳያችን ቀርቧል::

መልካም ዕይታ!

## Time for Cartoon Portraits

Welcome once again to another exciting month of appreciation of art and life at Galleria To.Mo.Ka. As we continue our journey of showcasing the best that Ethiopian artists have to offer, we invited Cartoon Portrait Artist Tedros Mesfin to grace our gallery.

Most people recognize the Cartoon Portraits of Teodros Mesfin; popularly known as Teddy Man in the social issue columns of the Amharic news papers including Ethio Channel and Yegna Press. He also showed his works in a number of exhibitions and left his own marks in the minds of art lovers in Ethiopia.

Teddy Man's unique take of art involving popular personalities from politics, media, sports and the entertainment sectors gives us a chance to look at them as one of our own and relatable to us. His cartoon arts accompanying serious social feature articles also initiate the appetite for reading.

We can not possibly describe the whole essences of the art works presented by Teddy Man. Instead, we invite to explore the works in your own time and imagination sipping your favorite To.Mo.Ka Coffee.

Enjoy!



ደስ ይለዋል:: ለዚህ እንዲያግዘውም የተለያዩ ሥልጠናዎችን ወስዷል:: በኢንፎኔት ኮሌጅ በዳይሬክቲንግ ዲፕሎማውን አግኝቷል:: ወደ ማስተር ፊልም ፕሮዳክሽን ትምህርት ቤት ጎራ ብሎም "ኤዲቲንግ ኦፍ ግራፊክስ"፣ በ "ግራፊክስ ዲዛይን"፣ እንዲሁም በፊልም ሥራ የተለያዩ ዲፕሎማዎችን አግኝቷል:: በቪዲዮ ቀረጻና ኤዲቲንግም ኮርሶችን በመውሰድ ከሰርግ ቀረጻ አንስቶ የፊልም ቀረጻንና ኤዲቲንግን ለተወሰነ ጊዜ ሰርቷል:: ከዚህ ቀደም "በራድ ፍም" የተሰኘ ፊልም ዳይሬክት ማድረጉን እንዲሁም በዚህ ወቅት አንድ አዲስ ፊልም እየሠራ እንደሚገኝ አጫውቶናል::

ናፍቆት ዮሴፍ

the list at the exhibition. 25 of the celebrities came to see their portraits and showed support to Teddy Man. The public also seemed to love it. Thousands of people visited the exhibition at the National Theatre Art Gallery after a warm opening ceremony at Jupiter Hotel in Addis Ababa.

Encouraged by his first exhibition reviews, Tewodros organized a similar exhibition last year featuring 35 celebrities and famous politicians including the portrait of U.S. President Barak Obama.

Teodros currently works as Cartoon Portrait Artist at the weekly Amharic newspaper Yegna Press. He hopes to do more of his portrait art and feature films.

Nebiyu Girma

| የሠዓሊው ማህደር: - ቴዎድሮስ መስፍን | Biography of the Painter- Teodros Mesfin |
|---|---|
| ሥራ፡ ካርቱኒስት | Occupation : Cartoon Portrait Artist |
| የትውልድ ዘመን፡ ሚያዝያ 16: 1967 ዓ.ም | Date of Birth : APRIL 25: 1974 G.C. |
| የትውልድ ቦታ፡ አዲስ አበባ | Place of Birth : Addis Ababa |
| የትምህርት ደረጃ፡ ዲፕሎማ (በድሮዊንግ)፣ ዲፕሎማ (በቪዲዮ እና በግራፊክ ዲዛይን)፣ ዲፕሎማ (በፊልም ዳይሬክቲንግ) | Education : Diploma (Drowing), Diploma (Video & Graphic Design), Diploma (filmmaking (Directing)) |

እየተመለከተም አደገ፡፡ ቴዲማን ወደ ሥዕል የተሳበበትን ምክንያትም ከዚሁ ጋር ያያይዘዋል፡፡ ወንድሞቹ የሳሉትን መልሶ ለመሳል ይጥር ነበር፡፡ የቴዲማን ወንድሞች ዛሬ ሥዕል ውስጥ አለመኖራቸው፤ በምትኩ እሱ በሞያው ዘልቆ እና ጠልቆ መገኘቱ ቴዲማንን ይገርመዋል፡፡ በካርቱን ፖርትሬይት ጥበብ የምናውቀው ቴዲማን ወደዚህ መንገድ ከመምጣቱ አስቀድሞ የሰዎችን ትክክለኛ ምስል ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ቴዲማን ለመጀመርያ ጊዜ የሥዕል ትርዒት ያቀረበው በኤርትራ ነበር፡፡ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከስደት ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ በአዲስ አበባ የሥዕል ትርዒት ለማቅረብ ግን ተቸግሮ እንደነበር ቴዲማን ይናገራል፡፡ ረጅም ጊዜም ወስዶበታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሰዎችን ምስል አዛንፎ ማቅረቡ ነበር፡፡ የሰዎችን ምስል አዛንፎ፤ ጆሮ አተልቆ፣ ዓይንን ባልተለመደ ዓይነት አስፈጥጦ ማቅረቡ በቀላሉ አልተወደደለትም፡፡ ይልቁንም በሰዎች ላይ እንደመሳለቅ፣ የሰዎችን ክብር እንደመንካት ተወስዶ ይተችም ነበር፡፡ ተቃውሞም አስተናግዷል፡፡ ከብዙ ፈተና በኋላ ግን የቴዲማን ህልምና ምኞት ሠመረ፡፡ ለአራት ዓመታት ከተፈተነ በኋላ ቦሌ በሚገኘው ጁፒተር ሆቴል የሰላሣ ሰዎችን ምሥል ይዞ ለመቅረብ ተሳካለት፡፡ የመጀመርያ የሥዕል ትርዒቱም ሆነ፡፡ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊን፣ የአትሌት ኃይሌ ገብረ ሥላሴን፣ የሌሎች ታዋቂ ኢትዮጵያዊያንን እና የራሱን ጨምሮ ቴዲ ማን ሰላሣ ሥራዎችን በዚህ የመጀመርያ የሥዕል ትርዒቱ አቅርቧል፡፡ በብሄራዊ ቲያትር እና በካፒታል ሆቴል ከዚያ በኋላ ያቀረባቸው ትርዒቶቹም ይጠቀሳሉ፡፡

ቴዲማን ከኅትመት ሚዲያው ጋርም በቅርበት ስሙ ይነሣል፡፡ የካርቱን ሥዕልን መሥራት የጀመረው "መዝናኛ " በተባለች ጋዜጣ ላይ ነበር፡፡ ከዚያ ለጥቆ በ"ኢትዮ ቻናል" አሁን ደግሞ በ" የኛ ፕሬስ" ጋዜጣ ላይ እየሠራ ይገኛል፡ ፡ ቴዲማን ከሥዕሉ ቀጥሎ ወደ ፊልም ጥበብ ገብቶ ቢሰራ

Yemen and Eritrea. He spent good number of years in these countries working different jobs. But he never forgot about his passion for painting and attended short trainings at different art schools. Tewodros also showcased his works in public exhibitions in Eritrea at one point.

After 10 years of leading a refuge life, he came back to Ethiopia some years ago.

Teodros also has the eye for cinema. In addition to his love for painting, he also wanted to know about films. Right after returning to Ethiopia, he went to film schools to study directing, graphics and editing and got certificates and diploma in film directing from Master Film Production and Infonet College. He used his skills to shoot and edit wedding videos. He also directed a movie titled "Berad Fim". He is now writing a film script to come back to the film industry.

Although he knew how to paint and had positive reviews, he got Cartoon Portrait Art when he was writing articles to newspapers. His Cartoon Portrait Art works were appreciated by readers of the newspapers at Meznagna and Ethio Channel newspapers, with some healthy dose of criticism. This feedback encouraged him to organize an exhibition featuring Cartoon portrait art of famous people in Ethiopia.

As this type of artistry was not common in Ethiopia, some of the celebrities whose portrait showed big ears, weird noses and distorted face features were uncomfortable being presented in such art forms. But the general feedback was positive. Former prime minister Meles Zenawi, Haile Gebreselassie, Meseret Defar, Tsedenia G/Markos, Sayat Demissie were just few of the celebrities whose portraits were included in



# ሥዕላዊ ስላቅ እና ሥዕላዊ ምጸት

ሠዓሊ ቴዎድሮስ መስፍን /ቴዲማን/ የግነተ ሥዕላዊ ቀልድና የግነተ ሥዕላዊ ምጸት /ካርቱን/ Cartoon ሠዓሊ ነው፡፡ ከሌሎች ሠዓልያን የሚለይበት ነገር ቢኖር፤ ሙያዬ ብሎ አዘውትሮና አከታትሎ መሣሉ ነው፡፡ በመስመራዊና በዝርጋዊ አሣሣል፤ በጥላና ብርሃን አወሳሰን በተለይም በወጣት ሴቶች ሕይወትና ኑሮ ላይ፤ ደጋግሞ የሣላቸውና የሚሥላቸው የሥዕላዊ ስላቅና የሥዕላዊ ምጸት ኪነ ንድፎች በብዙዎቻችን ዘንድ የታወቁ ናቸው፡፡

በቅድሚያ ስለ ሥዕላዊ ቀልድ /ካርቱን/ እና ስለ ሥዕላዊ ስላቅ/ ካሪኬቸር /Caricature/ ሥዕላት በጥቂቱ እንመልከት፡፡

ካርቱን /Cartoon/ በአንድ ነገረ ሐሳብ ወይም ጭብጥ ዙርያ፤ በጋዜጣዎችና በመጽሔቶች ላይ ለሚወጡ ጽሑፎች ፤በሥዕላዊ ቋንቋ ገላጭነቱ ታስቦ የሚሣል የኪነ-ንድፍ ሥዕላዊ ቀልድ ወይም ሥዕላዊ አስተያየት ነው፡፡ ካሪኬቸር /Caricature/ ደግሞ፤ እንደዚሁ በሥዕላዊ ቋንቋ አስቂኝነቱ ታስቦ በግነታዊ ወይም በኩሰሳዊ መልክ /በማግነን ወይም በማንኳሰስ / የሚሣል ሥዕላዊ ስላቅ ነው፡፡ ወይም ሥዕላዊ ምጸት ነው፡፡ ሥዕላዊ ሽሙጥ ወይም ሥዕላዊ አሽሙር ነው፡፡ ይህ አመለካከት በሠለጠነው የአውሮፓ ማህበረ ሰብ ሲታሰብና ሲገነዘቡት ነው፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ፤ እንዲህ በዕይታዊና በሥዕላዊ ቋንቋ አይገለጽ እንጂ፤ በንግግራዊ ቋንቋ በቃልና በጽሑፍ የሚገለጽ ቃላዊ ቀልድ ወይም አስተያየት ፤ ቃላዊ ሥላቅ፤ ወይም ቃላዊ ምጸት፤ ወይም ቃላዊ ሽሙጥ፤ የነበረና ያለ ነው፡፡ ይኸውም፡- የአንድን ሰው /ወንድ ወይም ሴት/ መልክአ ምስል፤ የፊት ገጽ ወይም የተክለ ሰውነትና አቋቋም ዓይቶ፤ ከሌላ የተፈጥሮ ወይም የሠው ሰራሽ ቁስ አካል ጋር በማመሳሰል፤ በንግግር ቋንቋ አግንኖ ወይም አንኳስሶ ስለምንነቱ መግለጽ ጥንታዊነት ያለው ሥነ ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አጭር ሰውን በማንኳሰስ ወይም በማግነን ‹‹የወንድ አጭር አውራ ዶሮ፤ የሴት አጭር ሴት ወይዘሮ››፤ ‹‹ቢወፍሩ ዘጦ፤ ቢከሱ ወረንጦ›› እያሉ መሳለቅና መሳቅ እጅግ የተለመደ ነው፡፡ አባባሉን ስንሰማ ደግሞ በእዝነ ኅሊናችን ሰሌዳ ላይ የሚያስቀረው ምናባዊ ምስል፤ የተለየ ሥዕላዊ ቀልድ ስላቅንና ምጸትን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ኢትዮጵያ በሥዕል ቋንቋ እንደ ቃለ ንግግር አግኖና አንኳሶ መሣል፤ የተለመደ አልነበረም፡፡ አይደለምም፡፡

ነገር ግን፤ ቀድሞ በዘመነ ኃይለ ሥላሴ፡- በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለአንዳንድ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ በዓላት መግለጫ የሚውሉ ግነታዊ ምስላት፤ በሥዕለ ቋንቋ ተሥለው ነበር፤ ብለን ለመናገር ባንደፍርም፤

# Cartoon and Caricature: Teodros Mesfin's Expressions

Teodros Mesfin is a Cartoon Portrait Artist. Unlike many artists who occasionally spend time with their passion, Teddy takes his work as a full time job. Most people in Ethiopia would recognize Teodros a.k.a. Teddy Man from Ethio Channel Newspaper. His drawings of women in different walks of life show irony in a cartoonic way that is unique to Teodros.

Cartoon by nature is an art form that accompanies articles written in newspapers or magazines to express the issues better, artistically. Cartoons may be used to initiate laughter but they also send critical messages in a sarcastic manner. This culture in the print media is very common in Europe and America.

Ethiopia's experience is a bit different. We use oral traditions to express dissatisfaction or happiness over something in sarcastic way. Most Ethiopians would find something equivalent in real life to contrast and express their views of disappointment in a funny but a tone of sarcasm.

Expressing views using Cartoons was not common in Ethiopia. But attempts were there in different newspapers and magazines. Asrat Weldemedhin and Zewdu Bekele are remembered from the

አንዳንድ ሠዓልያን በጥቂቱ እንደሞከሩ መጥቀሱ ግድ ይላል፡፡ ለምሳሌ፡- የሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ ተማሪዎች የነበሩት እነ ሠዓሊ አሥራት ወልደ መድኅን እና ሠዓሊ ዘውዱ በቀለ በቀድሞ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሥዕላዊ ቀልድ /Cartoon/ የተመላበት እንደሣሉ የሚታወስ ነው፡፡ በዘመነ ደርግ ዋዜማ ላይ ደግሞ፤ በጸደይ መጽሔት ላይ፤ ሠዓሊ በላይ ጎርፉ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ፤ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ በሥዕላዊ ሥላቅና በሥዕላዊ ምጸት አንኳስሶ በመሣል የዘመኑን አግራሞት አትርፎ ነበር፡፡ በዘመነ ኢህአዴግ ደግሞ፡- በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሄቶች ላይ የተለያዩ ብዙ ሠዓልያን በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ፤ በማህበራዊና በባህላዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሥሉት ሥዕላዊ ስላቅና ሥዕላዊ ምጸት፤ አንድም የተጋነኑ ሁለትም የተንኳሰሱ ኪነ ንድፎች እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በእነዚህ ዙርያ ለዓመታት በተከታታይ የሣሉ ወይም ሥለው ያቋረጡ ይገኛሉ፡፡ በተለይም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሠዓሊ ማኅሌት ወርቁ ትሥላቸው የነበሩት፤ የሥዕላዊ ስላቅና ምጸት፤ ኪነ ንድፎች በአንጻራዊነት በራሷ ንቃተ ኅሊና የተወሰኑና ዘይቤያዊ ነበሩ፡፡ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይም የሠዓሊ በቀለ ኃይሌ /አሁን በሕይወት የለም/ እና የሠዓሊ ኤልያስ አረዳ፤ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ የሠዓሊ ሠርጸ ድንግል ጣሰው፤ በመዝናኛ ጋዜጣ፤ በኢትዮ ቻናል ጋዜጣና በየኛ ፕሬስ ጋዜጣ ላይ ደግሞ ሠዓሊ ቴዎድሮስ መስፍን /ቴዲማን/ እና ሌሎችም፤ በፖለቲካዊ፤ በኢኮኖሚያዊ፤ በማኅበራዊና በባህላዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ የሣሉት የሥዕላዊ ስላቅና ምጸት ኪነ-ንድፎች ወዘተ ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ሠዓሊ ቴዎድሮስ /ቴዲማን/ ግን ሙያውን ወዶትና አምኖበት፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፤ ሙሉ ለሙሉ በግነተ ሥዕላዊ ቀልድ /ካርቱን/ Cartoon/ ላይ የተመሠረቱ ኪነ-ንድፎች በብሔራዊ ቴአትር አርት ጋለሪ በ2005 ዓ.ም፤ እንደገናም በካፒታል ሆቴል በ2007 ዓ.ም መጀመርያ ዓመት ላይ ያቀረባቸው የሥዕል ትርዒቶች አግራሞትን ያተረፉለት ናቸው፡፡ አሁንም በጋለሪያ ቶሞካ ያቀረባቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የታዋቂና የዝነኛ ሰዎች መልከአ ምስልን በግነተ ሥዕላዊ ቀልድ ዙርያ የሣላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያና እስካሁን ባለው መረጃ ሲታይ፤ በሀገራችን ሥራዬ ብሎ የሚሥል ሠዓሊ ቴዎድሮስ መስፍን /ቴዲማን/ ብቻ ነው፤ ለማለት ይቻላል ፡፡

በእርግጥ ሥዕላዊ ቀልድ ስላቅን እና ምጸትን /cartoon and caricature/ የተላበሱ ኪነ-ንድፎችን ለመሣል፤ ሦስት ዐበይት ጉዳዮች በሠዓሊው ላይ ወሳኝነት አላቸው፡፡ ይኸውም አንድ፡- የሠዓሊው ሥዕላዊ ዕውቀትና ክሂሎት በብቃት መሟላት፤ በተለይም የኪነ-ንድፍ ችሎታው፡፡ ሁለት፡- ሠዓሊው የሚኖርበትን ማኅበረሰብ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኹኔታ፤ በሚገባ የመረዳት፡፡ ሦስት፡- የሠዓሊው ግለኛ ባሕርይ በተለይም ለቀልዳዊ የስላቅና የምጸት ሕይወትና ትርጓሜ ያለው ነገረ ኅሊናዊ ዝግጅት በቀዳሚነት የሚፈለጉ ናቸው፡፡

ሠዓሊ ቴዎድሮስ /ቴዲማን/ ከእነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች የሚያሟላው እና የማያሟላው እንዳለ ይታወቃል፡፡ ጥያቄው ግን፤ ሙያውን ጠብቆና አክብሮ እስካሁን ድረስ በመሥራት ብቸኛው የግነተ ሥዕላዊ ቀልድ /Cartoon/ ሠዓሊ በመሆኑ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡ ወደፊት

time of Emperor Haileselassie for their Cartoons published in Addis Zemen Newspaper. We also remember Belay Gorfu later in the military regime for his caricatures on political and economic issues in Tsedey Magazine. More artists started doing cartoons in the past 20 years, commenting on various political, social and economic issues through their cartoons. Among them are Mahlet Worku of Addis Zemen, Bekele Haile and Elias Areda of the Reporter Newspaper and Sertsedingil Tassew of Addis Admas. This month's featured artist in Galleria TOMOCA. Tewodros Mesfin, a.k.a. Teddy Man is also widely known for his works at Ethio Channel and Yegna Press Newspapers.

Teddy Man's cartoon and Portraits were not restricted to newspapers. He organized two exhibitions to showcase his works in 2012 and 2014. This show at Galleria Tomoca is also similar in nature consisting Cartoon Portrait of famous personalities in Ethiopia and elsewhere in the world.

There are three key ingredients for an artist to excel in Cartoons and Caricature. Good knowledge and sense of art and humor, skills in drawing and up-to-date knowledge of the socio political situation of the country he/she lives in. Although there are some qualities that he has to full fill and be trained, Teddy Man strives to have qualities and use art as a medium to express important issues artistically. Of course, he is still in search of possessing all qualities, but he is probably the only one in Ethiopia who takes this work seriously to make it a full time job. He should be commended for hanging on his





## ቴዎድሮስ መስፍን

ተወልዶ ያደገው አዲስ አበባ ሜክሲኮ አካባቢ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በፍሬህይወት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤቶች ተከታትሏል፡፡ ቴዎድሮስ መስፍን (ቴዲማን)፡፡ የአሥራ ሁለተኛ ብሔራዊ ውጤቱን እንኳን ሳያይ ከሀገር ወጣ፡፡ የስደት ሕይወትንም ጀመረ፡፡ በስደት በቆየባቸው የአፍሪካ ሀገራት አጫጭር የሥነ ሥዕል ሥልጠናዎችን ወስዶ የተለያዩ ዲፕሎማዎችን እና የምስክር ወረቀቶችን አግኝቷል፡፡

ቴዎድሮስ መስፍን /ቴዲማን/ ለራሱ እንኳን በማይገባው ምክንያት ነበር ከአንድ አብሮ አደጉ ጋር ከሀገር የወጣው፡፡ የመጀመሪያ የስደት መዳረሻውም ኬንያ ነበረች፡፡ በዩጋንዳ፣ በሱዳን፣ በየመን፣ በመጨረሻም ለረጅም ጊዜ የቆየው በኤርትራ ነው፡፡ ቴዎድሮስ ከአሥር በላይ ለሆኑ ዓመታት የስደት ሕይወትን ከገፋ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡


ቴዲማን ሁለት ታላላቅ ወንድሞቹ ሥዕል ሲሠሩ እያየ አድጓል፡፡ የቴዲማን ወላጆች ሁለት ታላላቅ ወንድሞቹ ሠዓሊ እንዲሆኑ ይፈልጉ ነበር፡፡ የሥዕል መምህር ተቀጥሮላቸውም በቤት ውስጥ የሚማሩበትን ዘመን ቴዲማን ያስታውሳል፡፡ የታላላቅ ወንድሞቹን ሥዕላት

## Teodros Mesfin

Although he grew up watching his elder brothers draw pictures, he never thought he would end up being a Portrait Artist. His brothers are now in different professions, but he hang on and stayed in the world of art. Most people would recognize the name Teddy Man from his Cartoon characters in newspapers, and most recently in his Portrait Exhibitions of popular figures in Ethiopia and elsewhere in the world. This month , Galleria Tomoca brings you the amazing works of Tewodros Mesfin.

Teodros was born and raised in Addis Ababa around Mexico Square. He attended his elementary and Junior High at Firehiwot School and went to Shimelis Habte for his high school education. After taking his secondary school national examination, Tewodros left Ethiopia with his friend in search of better opportunities in neighboring Kenya without even looking at the results of his school leaving examination.

"I was young and did not think it through" recalls Tewodros. He crossed the Ethiopian border to get to Kenya at first and moved on to other countries including











ሁሉንም በሂደት ይበልጥ እንደሚያሚላ በመተማመን፤ በጋለሪያ ቶሞካ ያቀረበው የሥዕል ትርዒት፤ እስከዛሬ በጋለሪው ከታዩት በዓይነቱ የተለየ መሆኑን ከአድናቆት ጋር መግለጹ ተገቢ ነው፡፡ ግሩም ነው ቴዎድሮስ /ቴዲማን/፤ በርታ፡፡ ያበርታህ እላለሁ፡፡ የጥበብ ደጋፊነቱን ይበልጥ እያጎለበተ የመጣውን ጋለሪያ ቶሞካን፤ ከዘወትር ጣዕመ ቡናውና ስሉጥ መስተንግዶው ጋር እንዲቀጥል፤ ተመልካቹም ጣዕመ ቡናውን እያጣጣመና በግነተ ቀልዳዊ ስላቅ /caricature/ ኪነ-ሥዕላቱ እየተዝናና እንዲደሰት፤ በጎውን ኹሉ እየተመኘሁ፤ ከታላቅ ምስጋና ጋር በዚሁ አበቃለሁ፡፡

እሸቱ ጥሩነህ /ሠዓሊ/

ጥር ፳፻፯

passion and make life out of it.

Teddy Man featured unique art collections that keeps you think about issues in simple but profound way. I want to say Kudos to Teddy Man and look forward to see more of your work in the future.

Galleria Tomoca as usual has continued to support the art family in Ethiopia along with the excellent taste of its coffee. Keep up the good work!

Art lovers and enthusiasts, I invite you to enjoy and smile visiting Teddy Man's unique collections.

Eshetu Tiruneh (Painter)

January 2015